# ዘመነ ግርምቢጥ

(ከሣህሉ በቀለ)

እንዲህ አይደለም ወይ፤ ዘመነ ግርምቢጥ
ውሻ ወደግጦሽ፤ አህያ ወደ ሊጥ፡፡

የሕዝብ መሪዎቹ
ላገር ታጋዮቹ
ለመብት ለነፃነት፤ ለሠላም ሟቾቹ
ሲወርዱ ቃሊቲ፤ በወያኔዎቹ
ምን ማድረግ ይሻላል፤ ለማንስ ይጮኻል
የዘንድሮስ ነገር፤ ሆድ ያውቃል ሆድ ያውቃል፡፡

ፓርላማን ለከሀዲ፤ ቃሊቲን ላርበኛ
አሰብን ለገንጣይ፤ ባድመን ለዳኛ
ኢትዮጵያን ለውርደት፤ ባንዲራን ለመቀስ
አደረገውኮ፤ ጉዱ አቶ መለስ፡፡

እራሱ ፍርድ ቤት፤ እራሱ መርማሪ
እራሱ ደህንነት፤ እራሱ አሳሪ
የአቶ መለስ ሥራ፤ በጣም አስነዋሪ
ለኢትዮጵያም ላፍሪካም፤ ሆኗል አሳፋሪ፡፡

ወንድሜ ሥጋዬ፤ ክቡር አቶ መለስ
አንድ ቀን በታሪክ፤ መስሎት ማይከሰስ
የአበሻን ምድር፤ ሲመትር ሲቀንስ
እኔስ ፈራሁለት፤ ለሱ አጨራረስ፡፡

ስንዴ በልመና፤ ሰኳር በልመና
ዘይት በልመና፤ ኪኒን በልመና
እያግበሰበሰ፤ ታላቅ ለማኝ ሆኖ
ኢትዮጵያን ቆራርጦ፤ ከፋፍሎ፣ ሸንሽኖ
እስከ መቸ ይሆን፤ የሚኖረው ገኖ
ምናለ ቢጠፉ፤ እንደዱቄት በኖ፡፡

እንኳን አንተ ደሀው፤ በምፅዋት ኗሪ
ሀያል የነበሩት፤ እጅጉን አስፈሪ
ሂትለር፣ ሙሶሊኒ፣ ስታሊን፣ ቸቸስኮ
ሳዳም፣ ኢዲ አሚን፤ አሁን የሉምኮ፡፡

ሥልጣንና ገንዘብ፤ ውሸት ያሰከረው
ጥላቻና ተንኮል፤ እብሪት የወጠረው
እንዲህ አይነት መሪ፤ እንዲህ አይነት ንጉሥ
አይተን አናውቅም፤ ፍፁም እንደ መለስ፡፡

ቢሆንም አዳምጠኝ፤ መለስ ልምከርህ'
የያዝከው ጫወታ፤ ላይጠቅም ላይበጅህ'
ሺህ አመት ላትገዛ፤ ሺህ አመት ላትኖር
ምናለ ቢገባህ፤ የታሪክ ሚስጥር፡፡

ለሕይወትህ ፈርተህ፤ ከሕዝብ ተደብቀህ
ጥይት በማይበሳው፤ መኪና ተጭነህ
ከተራው ሕዝብ ጋራ፤ እንዲህ ተቃቅረህ
እንዴት ትዘልቃለህ፤ እንዴት ትኖራለህ?

ያመጣል ደብቁኝ፤ እዩኝ እዩኝ ማለት
ይኸኛው ቀን ሂዶ፤ ያኛው የመጣ ለት፡፡

የምንሞተው እኛ፤ የምትገለን አንተ
እሰረኞቹ እኛ፤ አሳሪያችን አንተ
ተበዳዮች እኛ፤ በዳያችን አንተ
ይህን ሁሉ ችለን፤ እርቀ ሠላም ስንል
ሳንበድል ሳንጎዳ፤ ፍዳ ሲደርስብን
ባለጊዜ ሆነህ፤ ፈላጭ ቆራጭ ጌታ
እንደ ፍርሀት ቆጥረህ፤ ያበሻን ዝምታ
ጨዋው የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ እንዲህ ሲንገላታ
መውደቂያህ አያምርም፤ የማታ የማታ፡፡

አውቆ ተኛ እንጂ፤  እንቅልፍ መች ወሰደው
ሠላም መረጠ እንጂ፤ አመፅ መች አቃተው
ይኸ ሁሉ ትግሥት፤ ፍርሀት ከመሰለው
የወያኔ ዕጣ፤ እንደ መንግሥቱ ነው፡፡

ሕዝቡ ከተቆጣ፤ ከታችም ከላይ
ሀይልን ከመረጠ፤ ለሠላም ታጋይ
ጥቁር ፀጉር ይብቀል፤ በምላሴ ላይ
ወያኔ ይጠፉል፤ ሳንሰማ ሳናይ፡፡

እርቀ ሠላም ማለት፤ ምንም ካልመሰለው
እሾህን በሾህ ነው፤ መንቀል የሚቻለው
ያበጠ ይፈንዳ፤ እውነቱ ይኸው ነው!